EDUCATIONAL CENTER

# የትምህርትና ሥልጠና ችግሮቻችን እና የመፍትሔ አቅጣጫዎች (ፍኖተ ካርታ) ግምገማ

## ክፍል ሁለት: **የትምህርት መዋቅር**

የግል አስተያየት

በነጋ ወርቁ ደበላ (ፕሮፌሰር)

©2019

critique

# Table of Contents


**የትምህርት መዋቅር** ..... 3
የዶክተር ነጋ የትምህርት ማእከል ..... 3
ቅድመ ኪንደርጋርተን (ፕሪኬ) 1 ሶስት አመት የሞላቸውን በተመለከተ፤ ..... 4
  በፌደራል መንግስት የትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ፤ ..... 4
ቅድመ ኪንደርጋርተን ፕሪኬ 2 (አራት አመት) ..... 5
ኪንደርጋርተንን (5 አመት የሞላቸውን)በተመለከተ፤ ..... 6
  በፌደራል መንግስት የትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ ..... 6
  በእስቴት ትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ፤ ..... 7
  በክፍል ደረጃ፤ ..... 8
References: ..... 9
አባሪ (Appendix): ..... 10
  አባሪ 1፡ ጎትቶ የመጣል ጨዋታ (Drag and Drop Game) ..... 10
  አባሪ 2፡ በማእከሉ የተዘጋጀ በነጠብጣብ ፎንት የተሰራ ቁጥር መጻፊያ ማስተማሪያ ..... 11
  አባሪ 3፡ ባለ ሁለት ቁዋንቁዋ (አማርኛና እንግሊዝኛ) ማስተማሪያ መጽሃፍ፣ጥያቄዎች ከነመልሳቸውና የምስክር ወረቀት ..... 12
  አባሪ 4፡ አሜሪካዊት ልጃገረድን ተከታታይ መጻህፍት ..... 16
  አባሪ 5: የንባብ ውድድር አውቶቡሶች ለቅድመ ኪንደርጋትን ተማሪዎች ..... 17


critique

# የትምህርት መዋቅር

ስለ ትምህርት መዋቅሩ ለውጥ ባጠቃላይ ሙሉ ለሙሉ ስስማማ፣ አንድ አመክሬና በጽናት አስረግጬ ለማለፍ የምፈልገው ነገር አለ።

ብዙ አገሮች የተጠኑ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት (አሜሪካንን ጨምሮ) በቅድመ መደበኛ ትምህርት እድሜ የሚገኙ ተማሪዎች የቅድመ መደበኛ ትምህርት ከተከታተሉ፤ የቅድመ መደበኛ ትምህርት የተማሩት ተማሪዎች ካልተከታተሉት ጋር ሲወዳደሩ የበለጠ ፈጣን የትምህርት እድገት እንደሚያሳዩ ይጠቁማሉ[1]። ይህንን አስመልክቶ ስለ አሜሪካ የቅድመ መደበኛ ትምህርት የተጻፈው፣ በአንድ ጸሃፊ አይን፣ ይህን ይመስላል። "ሁሉም ሰው የተስማማበት፣ ልጆች ማንበብ የሚገባቸው የእድሜ ወለል የለም፤ በዚህ በአሜሪካ አጥብቀን እንደምናምንበት፣ ልጆች አንደኛ ክፍል ወይም ስድስት አመት አካባቢ እንደምንለው"[2]።

አንድ ትልቅ ስራ መስራት የምንችልውና የወደፊቱን ትምህርት ትክክለኛ አቅጣጭ ማመልከት የምንችለው በቅድመ መደበኛ ትምህርት ላይ በደንብ ከሰራን ነው።

ቅድመ መደበኛን ትምህርት በሶስት ከፍዬ አቀርበዋለሁ - ቅድመ ኪንደርጋርተን (ፕሪኬ) 1 ሶስት አመት የሞላቸው ግን አራት ያልሆኑ ቅድመ ኪንደርጋርተን (ፕሪኬ 2) አራት አመት የሞላቸው ግን አምስት ያልሆኑ እና ኪንደርጋርተን (5 አመት የሞላቸው)። ይህ ትንታኔ መሰረት የሚያደርገው ላለፉት 5 አመታት በመቶዎቹ የሚቆጠሩትን ኢትዮ-አሜሪካውያንንና ሌሎቹንም በትምህርት ማእከል በማስተምርበት ጊዜ ካገኘሁት ልምድና ትምህርት ነው።

## የዶክተር ነጋ የትምህርት ማእከል

በቅድሚያ ስለ ዶክተር ነጋ የትምህርት ማእከል አንድ ሁለት ልናገር። ይህ የትምህርት ማእከል የተቋዋቋዋመው በ2013 ሲሆን ስራውን በይፋ የጀመረው በ ፌብሩዋሪ

critique

EDUCATIONAL CENTER

15፣ 2014 ነው። ይህ ማእከል ብዙ ተማሪዎችን ጥሩ ቦታ ያደረሰ ሲሆን ለተምሳሌነት ሁለት የጉዳይ ጥናቶችን (case studies) በአይናችሁ እንድታዩ አቀርብላችሁዋለሁ።

የማቀርባቸው ምሳሌዎች ከመጽሃፍ የተገለበጡ ሳይሆን በዚህ የትምህርት ማእከል ውስጥ በተግባር የተተረጎሙ ናቸው። በዚህ የትምህርት ማእከል ውስጥ የሚገኙ ህጻናትን ለምሳሌነት ማቅረብ እፈልጋለሁ። እነዚህን ለምሳሌነት አቀረብን እንጂ ሌሎችም ብዙ ህጻናት መልካም የሚባል የትምህርት ክሎአት አሳይተዋል። የእነዚህ ህጻናት ችሎታ በአሜሪካ እስታንዳርድ ድንቅ የሚያሰኙ ናቸው።

## ቅድመ ኪንደርጋርተን (ፕሪኬ) 1 ሶስት አመት የሞላቸውን በተመለከተ፤

በዚህ እድሜ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች ለማንበብ፣ ቁጥር ለመቁጠርና ሂሳብ ለማስላት እንዲሁም ስእል ለመቀባት የሚያስችል ችሎታ አላቸው። ኢንተር-አክቲቭ ወይም ሃሳብ ተመላላሽ ከሆኑ አፐሊኬሽንስ ወይም ፕሮግራሞች ጋር ተመላልሰው መግባባትና ጥያቄዎችን መመለስ ይችላሉ። እነዚህ ክሎቶች ለወዲፊቱ የትምህርት ጉዞአቸው እጅግ መሰረታዊ በመሆናቸው አውቀው እንዲያጠናክሩ መደረግ የሚገባውን እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

## በፌደራል መንግስት የትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ፤

1. በዚህ የእድሜ ክልል የሚገኙ ልጆች በጨዋታ ላይ የተገነባ ትምህርት በቀላሉ ሊስባቸው ስለሚችል፤ ይህን የሚያዘጋጁ የትምህርት ቴክኖሎጂ ሰዎችን በማወዳደር እንዲያዘጋጁ ማድረግ። ለስልክ፣ ለኮምፒውተር፣ ለታብሌት ቅርበት ያላቸው ልጆች የዚህ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ይሆናሉ። እኔ የሰራሁትን 'ጎትቶ የመጣል ጨዋታ' (drag and drop game) ኢትዮ-ኢዱኬሽን ድህረ-ገጽ ላይ ማየት ትችላላችሁ።

https://www.ethioeducation.com/%E1%88%83-%E1%88%86-%E1%8C%8E%E1%89%B5%E1%89%B6-%E1%8B%A8%E1%88%98%E1%8C%A3%E1%88%8D-%E1%8C%A8%E1%8B%8B%E1%89%B3-%E1%88%83-%E1%88%86-drag-and-drop-game/

ጨዋታውን ለማየት ጊዜ ከለሎት ደግሞ አባሪ (Appendix) 1ን፡ ጎትቶ የመጣል ጨዋታ (Drag and Drop Game) ስእልን ይመልከቱ።

2. ለአማርኛ ቋዋንቋዋ ዶትድ ወይም ነጠብጣብ ፎንት ፈልጌ ስላላገኘሁ፣ የለም ብዬ በማሰብ አሁንም በፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ ለአማርኛ ፊደላት ወይም ፎንት፣ የነጠብጣብ ፎንት (dotted fonts) የሚሰሩ ፕሮግራመሮች አወዳድሮ ማሰራት። የአማርኛ ጽሁፍን ለማስተማር በነጠብጣብና በቅድመ-ጽሁፍ ቅርሶች (prewriting skills) ክሎቶች መጀመሩ ተገቢ ነውና።

## ቅድመ ኪንደርጋርተን ፕሪኬ 2 (አራት አመት)

የተማሪዎችን የንባብ ችሎታና ፍላጎት ለማስጀመር መደረግ ያለበትን እርምጃዎች እንደሚከተለው አቀርባለሁ። በተፈጥሮ ችሎታ ያላቸውና በተለይም በአበልጻጊ አካባቢ (nurturing environment) ያደጉ ልጆች በዚህ ደረጃ ማንበብ ይችላሉ። የሶስት አመት ልጅ እራስዋን ስታስተዋውቅና ስታነብ ያለውን ቪዲዮ ሊንኩን በመጫን ይመልከቱ። ይህንን ለማየትና ለመስማት https://www.ethioeducation.com/ethioeducation-blog/

ወይም https://drnegaeducationcenter.org/publications/ ሄዳችሁ ሊንኩን ተጫኑት።

EDUCATIONAL CENTER

## ኪንደርጋርተንን (5 አመት የሞላቸውን)በተመለከተ፤

### በፌደራል መንግስት የትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ፤

መምህራንንና ደራሲያንን ጥያቄ ያላቸው መጻህፍትን እንዲያዘጋጁ የገንዘብ ሽልማት (ግራንት)ማዘጋጀት። ለምሳሌነት አባሪ 3፡ ባለ ሁለት ቋዋንቋዋ (አማርኛና እንግሊዝኛ) ማስተማሪያ መጽሃፍ፣ጥያቄዎች ከነመልሳቸውና የምስክር ወረቀት

ይመልከቱ። (ይህን መጽሃፍ በነጻ ነው ያዘጋጀሁትና ለቅድስት ማሪያም ዩኒቨርሲቲ እንዲያትሙት የሰጠሁት።)በዚህ መጽሃፍ ላይ እንደሚታየው ህጻናትን ሁለት ቋዋንቋዋ (አማርኛና እንግሊዝኛ) በማስተማር በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ እንደመጣል ይቆጠራል። ይህ መጽሃፍ ወደ አፋን ኦሮሞ እንደተተረጎመም አታሚዎቹ አስታውቀውኛል። ቅጅውንም አይቼዋለሁ።

በዚህ ደረጃ የሚጻፉ መጽሃፍቶች ከብሄራዊ ማንነት (ethnic identity) በላቁ እሴቶች (ultra-ethnic values) ላይ ቢያተኩሩ መጪው ትውልድ ተዋዶ፣ ተከባብሮ አንድነቱን አስከብሮ፣ አንድነትን ከብዙሃንነት ጋር አዋቅሮ ማስኬድ ይቻላል። እንደ ጃንጥላ (ጃንጥላ በስሩ የተጠለሉትን ሁሉ ከጸሃይና ከዝናብ እንደሚከላከል ሁሉ) ሁሉን አቃፊ፣ ሁሉን በእኩልነት፣ በአንድነት፣ በትብብርና በባህርይ ጥራት (character) በሆኑ እሴቶች ላይ ያተኩሩ መጣጥፎች የጋራ እሴቶች ላይ እንድንግባባ ስለሚያደርጉ ልጆቻችንና መጪው ትውልድ

የማይናቆርበት አገር እንዲኖሩ አስተዋጾ ይኖረዋል። ለሁሉም ልክ እንደጥላው ደህንነትን፣ መብትን፣ ጥቅምን፣ ነጻነትን፣ አብሮ መኖርን፤ በአገሪቱ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ፣ የጾታ፣ የእድሜ፣ የቋዋንቋዋ፣ የባህል ልዩነቶች ላይ ሳያተኩር ያለአድሎ ለሁሉም በአለኝነት የሚቆሙ ሰብአዊና ኢትዮጵያዊ እሴቶችን ይጨምራል።

## በእስቴት ትምህርት ሚኒስቴር ደረጃ፤

እኛ ዳይአስፖራ ኢትዮጵያውያን ባልተወለድንበትና ባላደግንበት አገሮች በሰላም ትምህርት ተምረን፣ ትዳር መስርተን፣ ልጆች ወልደን፣ አስተምረን፣ ንብረት አፍርተን በፈለግንበት ሰአት የፈለግንበት ቦታ መኖር ስንችል፤ ኢትዮጵያዊው በአገሩ ይህን ማረግ አለመቻሉ በትምህርት ላይ እጅግ መስራት እንዳለብን አመልካች ነው። የምንጽፋቸውም መጻህፍት በነዚህ እሴቶች ላይ ተመርኩዞ፣ አብሮ መኖርን፣ በትዳር፣ በሰርግ፣ በሃዘን፣ በደስታ፣ በበአል፣ በስራ እንዴት እንደተሳሰርን በትርክት መልክ ለአዲሱ ትውልድ ማስተማሩ፤ ዘለቄታዊ መፍትሄ በረጂም ጊዜ ሊያመጣ ይችላል። ጎረቤት ማለት ከዘመድ በላይ በክፉ ጊዜ በቶሎ የሚደርስ አጋር መሆኑን የሚያስተምር ይዘት ያላቸው ጽሁፎች ለንባብ ማብቃት አብሮነትንና ያጎለብታል። በተመጣጣኙ ደግሞ ለምሳሌ በአሜሪካ፣ 'አሜሪካዊቱዋ ልጃገረድ' ((አባሪ 4ትን፡ አሜሪካዊት ልጃገረድን ተከታታይ መጻህፍት ይመልከቱ)) በሚል ተከታታይ እትመት (series) የሚታተሙትን አንድነትን ከብዙሃንነት ጋር ያጣመሩትን (unity in diversity) ድርሰቶች ማንበቡ፣ የልጅ ልጆቻችን በደንብ ተግባብተውና ተረዳድተው በፍቅር እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል ባይ ነኝ። ስለሌላው ባህል፣ ሃይማኖት፣ የኑሮ ዘይቤ፣ ምግብ፣ ቋዋንቋዋ፣ አለባበስ፤ መማር ማወቅ ፍቅርንና አብሮነትን ያጎለብታል በብዙሃንነት ላይ የተመሰረተ አንድነትን ይፈጥራል። ከራስ ውጭ ሌላውን ማወቅ፣ ማዳመጥ፣ መረዳት፣ ማክበር፣ ከልዩነት ይልቅ ተመሳሳይነትና አብሮነት ላይ ያተኮረ ሌላውን እንደራስ የሚያዩበት ድርሰቶች ካነበቡና ከተተረከላቸው፣ ልጆቻችንና ተተኪው ትውልድ አርቆ ተመልካችነትና ተረጂነትን በልጅነት ካወቁ በጎልማሳነት ጊዜ ነገሮችን ለመረዳት ችግር አይገጥማቸውም። አለም በቴክኖሎጂ እየጠበበች በሄደችበት ጊዜ ጎረቤትን አለማወቅ ለመጪው ትውልድ

የሚጠቅመው አይሆንም። ጅጅጋ፣ ሃረርና ድሬደዋን በመሰሉ ህብረ ብሄራዊ ከተሞች የተወለድንና ያደግን ይህንን ገና በጨቅላ እድሜያችን ነው ተምረን ባለ ሁለትና ሶስት ቋንቋዎች ተናጋሪ (multi-lingual) ህብረ ባህላዊ (multicultural) የሆነው።


## በክፍል ደረጃ፤

የተማሪዎችን የንባብ ችሎታና ፍላጎት ለማስጀመር  መደረግ ያለበትን እርምጃዎች እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

ኢትዮጵያ  ውስጥ ለቅድመ መደበኛ ደረጃ (ቅድመ ኪንደርጋርተን እና ፕሪ እስኩል) ሊደረጉ የሚችሉ፣ አሁን በትምህርት ማእከል ደረጃ እያደረግን ያለውን ልምድ ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ። ለቅድመ መደበኛ ደረጃ ተማሪዎች 37 ደረጃ ያላቸው የንባብ እርከኖችን አዘጋጅተን እያንዳንዱን እርከን ሲያልፉ በስማቸው የምትጠራውን አውቶቡስ አንድ እርምጃ/እርከን እናስኬዳታለን (አባሪ 5ትን ይመልከቱ)። ይህ ተማሪዎችን በከፍተኛ ሁኔታ እንዲነቃቁ ያደርጋል፣ የጤናማ ውድድር መንፈስንም ያጎለብታል። ስኬታማ አስተማሪነት ማለት ለመማር የተዘጋጀውን ተማሪ ማስተማር ብቻ ሳይሆን ያልተዘጋጀን ተማሪን በማነቃቃት ትምህርት መቀበል እንዲችል ማድረግም ነው። ያልተነቃቃን ተማሪን ማስተማር ከባድ ስለሆነ ውስጣዊ የመማር ፍላጎት ይኖረው ዘንድ ለአይን፣ ለጆሮ ለአእምሮው የሚስቡ ነገሮች ማዘጋጀቱ የትምህርት ሂደቱን የተሳለጠ ያደርገዋል። የቅድመ ኪንደርጋርትና ቅድመ መደበኛ ተማሪዎች አንብበው ፈተና እንዲወስዱ ያዘጋጀሁትን የ 110 መጽሃፍ የቴስት ባንክ ለማየት ተመዝግበው ሬጅስተር በመሆን ማየት ይችላሉ።

http://www.blackboard.com/coursesites/?sig=FRuzBDT7C9VOl3fX1Iobbwuk6VE%3D&courseId=_238685_1&timestamp=1560914580&inviteId=BB%253FBB_Cah0luIXHaeobSvefAoLPoV4UzGxD1z5nG9gUEbCBK8tUG%252B4ivX5lA%253D%253D

አንዴ ከተመዘገቡ በሁዋላ ኮርስስ የሚለውን ክሊክ ያርጉ።.




# References:

[1]Extract from Living and Working in America. https://www.justlanded.com/english/United-States/USA-Guide/Education/Pre-school-education

[2]https://www.todaysparent.com/family/activities/right-age-to-read/

critique

# አባሪ (Appendix):

## አባሪ 1፡ ጎትቶ የመጣል ጨዋታ (Drag and Drop Game)

**ጎትቶ መጣል ጨዋታ (Drag and Drop Game)**




**ሃ- ሃገር**




**ሄ- ሄደ**



**ህ- ህዝብ**

**(hezb)** **(hager)** **(hede)**

# አባሪ 2፡ በማእከሉ የተዘጋጀ በነጠብጣብ ፎንት የተሰራ ቁጥር መጻፊያ ማስተማሪያ


Dr. Nega's Educational Center


TRACEABLE NUMBERS

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 4 |
| 5 | 6 | 7 | 8 |
| 9 | 10 | 11 | 12 |

Dr. Nega's

EDUCATIONAL CENTER

# አባሪ 3፡ ባለ ሁለት ቋዋንቋዋ (አማርኛና እንግሊዝኛ) ማስተማሪያ መጽሃፍ፣ ጥያቄዎች ከነመልሳቸውና የምስክር ወረቀት



EDUCATIONAL CENTER

# ጥያቄ

ኢትዮጵያ ዋና ከተማ ማን ይባላል?

ሀ. አዲስ አበባ

ለ. ድሬዳዋ

ሐ. ጅጅጋ

ጌታቸው ወንድም ማን ይባላል?

ሀ. አበበ

ለ. ተስፋ

ሐ. ሻውል

የተወለደችው ልጅ ሴት መሆኑዋን ሲያውቅ ጌታቸው ምን አደረገ?

ሀ. ከቤት ጠፋ

ለ. በደስታ ዘለለ

ሐ. መፅሐፍ አነበበ

፲፱

# Quiz

1. What is the capital city of Ethiopia?
   a) Addis Ababa
   b) Dire Dawa
   c)Jijiga
2. What is the name of Getachew's little Brother?
   a) Abebe
   b) Tesfa
   c) Shawle
3. What did Getachew do when he found out that the newly born baby was a girl?
   a) Ran away
   b) Jumped with joy
   c)Read a book

19

4. የጌታቸው እናት ማን ይባላሉ?
   - ሀ. ብዙነሽ
   - ለ. ደብሬ
   - ሐ. አባይነሽ

5. የጌታቸው እናት ወንድ ልጅ ከወለድኩ ለቤተክርስቲያን እሰጣለሁ ያሉት ስለት ምን ነበር?
   - ሀ. የወርቅ ኩባያ
   - ለ. ገንዘብ
   - ሐ. ጥላ

መልስ

1.ሀ  2. ለ  3. ሀ  4. ሀ  5. ሐ




4. What is the name of Getachew's mother?
   - a) Bizunesh
   - b) Debre
   - c) Abaynesh

5. What did Getachew's mom promise to bring to church if God gave her a baby boy?
   - a) A gold Cup
   - b) Money
   - c)An Umbrella

Answer:


1.a  2.b  3. a  4. a  5. c


የምስክር ወረቀት
This Certificate is proudly presented to
[Name]
For successfully reading this book,
Taking the quiz
And scoring ___%
Dated this ___ day of ___, 20__
Guardian/Parent
Signature
21

# አባሪ 4፡' አሜሪካዊት ልጃገረድ' ተከታታይ መጻህፍት



# አባሪ 5: የንባብ ውድድር አውቶቡሶች ለቅድመ ኪንደርጋትን ተማሪዎች



Dr. Nega's

EDUCATIONAL CENTER

